

# ኤልያስ

- አክአብ በእስራኤል ምድር ከተነሱት ክፉ ነገስታት መካከል አንደኛው ነበር። ኤልያስ ደግሞ አክአብ በነገሰበት ዘመን ሲያገለግል የነበረ ነቢይ ነው።

- አንድ ቀን ኤልያስ ንጉሱን ሊጎበኝ ሄደ። በምድረ እስራኤል ለተወሰኑ አመታት ዝናብ እንደማይኖር እግዚአብሔር መናገሩን ለአክአብ አሳወቀው። በዚህም አክአብ በኤልያስ ላይ እንደሚቆጣ እግዚአብሔር ያውቅ ስለነበር ኤልያስን በዮርዳኖስ ወንዝ አጠገብ ደበቀው። በየዕለቱም ኤልያስን የሚመግቡ ቁራዎችን ምግብ እያስያዘ ወደኤልያስ ይልክ ነበር።

- ልክ ኤልያስ እንደተናገረም በእስራኤል ምድር ለሶስት ዓመታት ዝናብ አልነበረም።

- በመጨረሻም እግዚአብሔር ኤልያስን “ሂድና ለአክአብ ተገለጥ፤ እኔ ዝናብን እልካለሁ።” አለው። ከዚህ በኋላም ኤልያስ አክአብን 450 የሐሰተኛው የበዓል ነቢያትን ወደ ቀርሜሎስ ተራራ ከእርሱ ጋር ይወራረዱ ዘንድ እንዲልካቸው ጠየቀው። የበዓል ነቢያትም መሰዊያ አዘጋጁ፤ በመሰዊያው ላይም ያረዱትን በሬ ስጋ አስቀመጡበት። ከዚያም አምላካቸው በዓል እሳት አውርዶ መስዋዕታቸውን እንዲያቃጥል ወደአምላካቸው ጮኹ። የሆነ ነገር ግን አልነበረም።

- ኤልያስም እንዲሁ መሰዊያን አዘጋጀ። እርሱም ባዘጋጀው መሰዊያ ላይ ያረደውን በሬ ስጋ አስቀመጠ። በመሰዊያው ላይም በ12 ትልልቅ እንስራዎች ውኃ ሞልቶ በመሰዊያው ላይ አፈሰሰበት። ከዚያም እግዚአብሔርን እሳት ከሰማይ እንዲያወርድና መስዋእቱን እንዲያቃጥል ለመነው። እግዚአብሔርም የኤልያስን ልመና ሰምቶ መስዋዕቱን፣ መሰዊያውንና መሰዊያው የተሰራበትን ድንጋይ ጭምር አቃጠለው። በጣም የሚገርመውም በመሰዊያው ላይ የነበረው ውኃ እንኳን ሳይቀር በእሳቱ መቃጠሉ ነበር። ከዚያም ሕዝቡ ሁሉ እግዚአብሔርን ማክበርና ማምለክ ጀመሩ።

*ይህ የኤልያስ ታሪክ የሚገኘው በብሉይ ኪዳን በ1ኛ ነገስት ምዕራፍ 17 እና ምዕራፍ 18 ውስጥ ነው።*

http://gardenofpraise.com